# Asylum Advice

## ድህረ ውሳኔዎች - የጥያቄ ውድቅ መደረግ

# ድህረ ውሳኔዎች - የጥያቄ ውድቅ መደረግ

በዚህ ክፍል የጥገኝነት ጥያቄህ ውድቅ ከተደረገ ምን ሊያጋጥም እንደሚችል በዝርዝር ቀርቧል። የጥገኝነት ማመልከቻህን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ካሉህ ጥያቄዎቹን የምክር አገልግሎት ለሚሰጥህ የህግ አማካሪ ማቅረብና መወያየት አለብህ።

## 4B.1 አቤቱታህ ውድቅ ከተደረገ በኋላ የሚኖሩ አማራጮች

የጥገኝነት ቃለ መጠይቅ ካደረግህ በኋላ Home Office የጥገኝነት ጥያቄህን ውድቅ የሚያደርግ ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል። Home Office ባስተላለፈው ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለህ። Home Office ጥያቄህን ውድቅ ካደረገው አሉኝ የሚላቸውን ምክንያች የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣል። ደብዳቤው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚጻፍ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘኸው በደንዳቤው ይዘት ዙሪያ ከህግ አማካሪህ ጋር መወያየት አለብህ። Home Office የስደተኝነት ወይም የሰብዓዊ ጥበቃ መስፈርቶችን ለማሟላት አትችልም ብሎ እንዲያምን ምክንያቱ ምን እንደሆነ በደብዳቤው ይገለጻል።በዚህ ደረጃ ላይ ያሉህን አማራጮች በጥንቃቄ መመርመር ይኖርብሃል።

የሚከተሉት አማራጮች አሉህ፡-

- Home Office ባስተላለፈው ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት ሊኖርህ ይችላል። ይህም ሲባል ከ Home Office ነጻ የሆኑ፤ ውሳኔውን እንደገና በመመርመር በውሳኔው ይስማሙ እንደሆነና እንዳልሆነ የመወሰን ስልጣን ያላቸው የኢሚግሬሽን ዳኛ ጉዳዩን እንዲያዩት ልትጠይቅ ትችላለህ። በዚህ ዙሪያ ከህግ አማካሪህ ጋር መወያየት አለብህ። Home Office ባስተላለፈው ውሳኔ ላይ የይግባኝ አቤቱታ የምታቀርብበት የጊዜ ገደብ እንዳለ እባክዎን ያስታውሱ።

- የተረጋገጠ እምቢታ "certified refusal" ወይም የሚል ውሳኔ ከደረሰህ በቀጥታ ይግባኝ የማቅረብ መብት የለህም ማለት ነው። ቢሆንም ግን የፍርድ ሂደት ማጣሪያ እንዲደረግልህ ማመልከት ትችላለህ። በዚህ ዙሪያ ከህግ አማካሪህ ጋር መወያየት አለብህ።የህግ አማካሪው የፍርድ ሂደት ማጣሪያ እንዲደረግ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችለው ይህንን ለማድረግ በቂ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው።

- ይግባኝ ለማለት ካልፈለግህ ቀጥሎ የሚኖርህ አማራጭ እርዳታ የሚገኝበት በፈቃደኝነት ወደ ሃገር የመመለስ ማዕቀፍ Assisted Voluntary Return (AVR) (አሲስትድ ቮለንታሪ ሪተርን) ዩናይትድ ኪንግደምን (UK) ለቀው ለመሄድ የሚረዱ ናቸው እና ከነሱ ጋር መገናኘት ጠቃሚ ነው። ይህ እርዳታ የሚገኝበት በፈቃደኝነት ወደ ሃገር የመመለስ ማዕቀፍ Assisted Voluntary Return (AVR) (አሲስትድ ቮለንታሪ ሪተርን) በ Home Office (ሆም ኦፊስ) ስር የሚሰር ድርጅ ጋር ተገናኙ። ተጨማሪ መረጃ ካስፈለጋችሁ ከ www.gov.uk/return-home-voluntarily የሚል ዌብ ሳይት ይመለከትቱ እና ከ Voluntary Departures Team (በፍላጎት ወደ ሃገር ቤት መመልስ) የሚረዳ ብድን ጋር ተገናኙ 0300 004 0202።

## 4B.2 ምርጫህ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ ከሆነ

ጉዳይህ በ Home Office ውድቅ ከተደረገና ይግባኝ በማቅረብ መብትህ ለመጠቀም ከወሰንክ ጥያቄህ ውድቅ እንደተደረገ ማስታወቂያ እንደደረሰህ በተቻለህ ፍጥነት ከህግ አማካሪህ ጋር በመገናኘት መመካከር ይኖርብሃል። ውድቅ በተደረገው ጉዳይ ዙሪያ ለመወያየትና ይግባኝ የሚቀርብባቸውን ምክንያቶች ለማዘጋጀት ቀጠሮ መያዝ ይኖርባችኋል።
በህግ አገልግሎት ድጋፍ አማካኝነት (የህግ አገልግሎት ወጪ እገዛ በሚያደርግ) ጉዳይህን የሚይዝልህ የህግ ጠበቃ እንዲኖርህ ለማድረግ የገቢ መጠንህ ዝቅተኛ እንደሆነና ጉዳይህ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት ተጨባጭ እድል እንዳለው ማሳየት ይኖርብሃል። ይህም ማለት ነጻ የህግ አገልግሎት ድጋፍ ሊሰጥህ የሚችለው ጉዳይህ ተቀባይነት ለማግኘት ያለው እድል 50% ወይም የበለጠ ከሆነ ብቻ ነው። ይህንን በተመለከተ የህግ አማካሪህ የሞያው መለኪያዎችን በመጠቀም ግምገማውን ያደርጋል። የሚደረገውን ማጣሪያ ካላለፍክ ነጻ የህግ አገልግሎት የማግኘት ጥያቄህ ውድቅ ይደረጋል።

## 4B.3 ነጻ የህግ አገልግሎት የማግኘት ጥያቄዬ ውድቅ ከተደረገስ?

አንተ ወይም የህግ አማካሪህ ነጻ የህግ አገልግሎት የማግኘት ጥያቄህ ውድቅ የማድረግ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ መጠየቅ ትችላላችሁ። ነጻ የህግ አገልግሎት የማግኘት ጥያቄ ውድቅ መደረግ ላይ እንዴት ይግባኝ እንደሚባል እባክህን የህግ አማካሪህን አነጋግር።

ነጻ የህግ አገልግሎት ማግኘት ካልቻልክና የህግ አማካሪህ በግሉ ሊሰራልህ የሚችል ከሆነ ለህግ አገልግሎቱ ክፍያውን የምትከፍለው አንተው ራስህ ነህ። ጠበቆቹ በግላቸው ላንተ መስራት ከመጀመራቸው በፊት የስራውን የውል ሁኔታዎችና ነጥቦችን ላናተ ምግለጽና አንተም በቀረቡት ሁኔታዎች መስማማት አለብህ።

ነጻ የህግ አገልግሎት የማግኘት ጥያቄህ ውድቅ ከተደረገና ለዚህ የሚያስፈልገውን ክፍያ መክፈል የማትችል ከሆንክ ምርጫህ እስከሆነ ድረስ ራስህን ወክለህ መከራከር ትችላለህ።

## 4B.4 የይግባኝ ችሎት -

የይግባኝ ችሎት በጥገኝነትና ኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት (Asylum Immigration Tribunal, AIT) ይታያል። የይግባኝ ማመልከቻህ ሲቀርብ ጉዳይህ የሚታየው በየትኛው ፍርድ ቤት ችሎት እንደሆነ ማስታወቂያ ይደርስሃል። ሁለት ችሎቶች አሉ፤ እነሱም የመጀመሪያ ደረጃ ችሎትና ከፍተኛ ችሎት ናቸው። በእያንዳንዱ ፍርድ ቤት ውስጥ የኢሚግሬሽንና የጥገኝነት ክፍል አለ። ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ብዙ ፍርድ ቤቶች አሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ተግባር በ Home Office የተላለፉ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎችን መመርመርና ውሳኔ ማስተላለፍ ነው።

ይግባኝህ የሚታይበት ቀን ሲወሰን የፍርድ ቤቱ ችሎት የሚታይበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይደርስሃል። በ Home Office ድጋፍ የሚደረግልህ ከሆነ የመጓጓዣ ወጪህ እንዲሸፈንልህ ማመልከት ትችላለህ። ችሎቱ የተቀጠረበትን ዝርዝር የሚገልጽ ደብዳቤ ግልባጭን በመላክ የጉዞ ትኬት ወጪ ድጋፍ መጠየቅ ይቻላል። ይህንንም በተቻለህ ፍጥነት መፈጸም አለብህ። Asylum Help (አሳይለም ሄልፕ) የሚባል ድርጅግ ስለዚህ ንገሮች ሊረዳችሁ

ይችላል፡ እባካችሁ በዚህ ስልክ ቁጥር ደውላችሁ 0808 8000 622 የሆነ እርዳታ ካስፈለጋችሁ ልትገናኙን ትችላላችሁ።

የጥገኝነትና ኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት (AIT) ዋነኛ ክርክር ከመደረጉ በፊት (በማንኛውም ሰዓት) ውስብስብ በሆኑ ጉዳዮች የተነሳ ጉዳዩ ላይ ሊወስንና ጉዳዩ ለኢሚግሬሽን ፓነል ወይም ለከፍተኛ የኢሚግሬሽኝ ዳኛ ቀርቦ ሊታይ ይችላል።

ጉዳዩ በሚታይበት ቦታ ችሎቱ ከሚከፈትበት ጊዜ ከ 30 ደቂቃ በፊት አስቀድመህ መገኘት ጠቃሚ ነው። የደህንነት ፍተሻን ማለፍና ችሎቱ የሚሰየምበት ክፍል የትኛው እንደሆነ ማወቅ አለብህ። ችሎቱ በሚታይበት ጊዜ የሚከተሉት ሰዎች በክፍሉ ውስጥ ይገኛሉ፡-

- የኢሚግሬሽን ዳኞች፣ በክፍሉ ውስጥ ከፍ ባለ ቦታ ፊት ለፊት ይቀመጣሉ። ችሎቱን እየመሩ ጉዳይህን በተመለከተ አንተን፣ የህግ አማካሪህንና Home Officeን በመወከል የቀረበ ኦፊርን ይጠይቃሉ።
- Home Office ተወካይ ኦፊሰር፡-Home Office ስላንተ ጉዳይ ያላቸውን አቋም የሚገልጽና UK ውስጥ እንድትኖር ፈቃድ ያልተሰጠህ በምን ምክንያቶች እንደሆነ የሚያስረዳ ተወካያቸውን ይልካሉ።
- ምስክሮች፣በጉዳይህ ላይ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ የተጠሩ ማናቸውም ምስክሮች።
- የፍርድ ቤት አስተርጓሚ፣አስተርጓሚ እንዲቀርብልህ ከጠየቅህ ዳኛው የሚቀርቡልህን ማናቸውም ጥያቄዎችንና የምትሰጣቸውን ምላሾች የሚተረጉም አስተርጓሚ ይኖራል። የምትናገረውን ነገር በትክክል በመተርጎም Home Office ስላቀረብካቸው መረጃዎች ሙሉ ሪከርድ እንዲኖረው ማድረግ አለባቸው።

አስተርጓሚዎች አንተ የምትሰጣቸውን መረጃዎች ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። አስተርጓሚውን በተመለከተ ማንኛውም ቅሬታ ካለዎት የንግግር ዘዬዎን ወይም አካባቢያዊ የቋንቋ አጠቃቀምዎን ሙሉ ለሙሉ የማይረዳ ከሆነ ጥያቄዉን በተቻለ ፍጥነት ወዲያውኑ ለህግ አማካሪዎ ለኢሚግሬሽን ዳኛው ማሳወቅ አለብዎት። ጉዳይዎ ላይ በሚወሰነው ውሳኔ ወይም በውጤቱ ላይ ተጽእኖ አያሳድርም።

የፍርድ ቤት ክፍሎች ለህዝብ ክፍት የሆኑ ቦታዎች በመሆናቸው በክፍሉ ውስጥ ሌሎች ሰዎችም ሊገኙ ይችላሉ።

## 4B.5 የፍርድ ቤት ቀጠሮዎች

ጉዳዩ የሚታይበት ቀን ከተወሰነ በኋላና ይህ ቀን ከመድረሱ በፊት ጉዳዩ እንዲታይ የሚፈልጉበትን ቀን (የቀጠሮ ማስተላለፍን) የሚመለከት ጥያቄን አንተ ወይም የህግ ጠበቃህ ለ AIT ማቅረብ ትችላላችሁ። ጥያቄው ለጉዳይ አስተዳደር ማጣሪያ ችሎት ይቀርባል። አንተ ወይም የህግ ጠበቃህ ይግባኙን የሚደግፍ ማስረጃን (ለምሳሌ የህክምና ሪፖርት ወይም ውጭ ሃገር ያሉ ሰነዶች) ለማሰባሰብ ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልገናል የሚል ክርክር ማቅረብ ትችላላችሁ።

የይግባኝ ችሎት እየታየ እያለ ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልገው ጉዳይ ከተገኘ ዳኛው፣ Home Office ወይም የህግ አማካሪህ ተጨማሪ ቀጠሮ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ለጉዳህ ጠቃሚ ይሆናሉ ብለህ የምታስባቸው ሰነዶች ትውልድ ሀገርህ ውስጥ ካሉህ በተቻለህ ፍጥነት ይህን በተመለከተ ከህግ አማካሪህ ጋር መወያየት አለብህ። ይህንን ማድረግ ባንተ ወይም በቤተሰብህ ደህንነት ላይ ችግር የማያስከትል ከሆነ እነዚህ ሰነዶች ወደዚህ የሚመጡበትን ሁኔታ እስክታመቻች ድረስ ጉዳዩ ሳይታይ እንዲቆይ ሊደረግ የሚችልበት እድል አለ።

ዳኛው ለጉዳዩ ቀጠሮ ለመስጠት ከወሰኑ ሌላ የቀጠሮ ቀን ይሰጣል። ልዩ ሁኔታዎች ካልኖሩ በስተቀር ይህ ቀጠሮ የመጀመሪያው ቀጠሮ ከተቀጠረበት በኋላ 28 ቀን የበለጠ መሆን የለበትም።

ዳኛው ቀጠሮውን ላስተላልፉና በቀጠሮ ቀን በችሎት ላይ መገኘት ለኖርብህ ይችላል። በቀጠሮው ቀን በችሎት ላይ ካልተገኘህ አንተ ባልተገኘህበት ችሎት ውሳኔ ሊተላለፍ ይችላል።

## 4B.6 የይግባኝ ችሎት በሚታይበት ወቅት

ዳኛው ለሚያቀርበው ጥያቄ ሙሉ መልስና በተቻለህ መጠን ብዙ መረጃዎችን መስጠት አለብህ። ዳኛው፣ የህግ አማካሪህ እና የHome Office ተወካዩ ህጉ ባንተ ጉዳይ ላይ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ይወያያሉ።

በአንዳንድ ጉዳዮች ዙሪያ፤ በተለይም በግላዊ ወይም ስሜትን ስለሚነኩ ጉዳዮች መናገር ላትፈልግ ትችላለህ ቢሆንም ግን ብዙውን ግዜ ልትናገራቸው የማንፈልጋቸው ነገሮች ማመልከቻህ ተቀባይነት እንዲያገኝ ወሳኝ ማስረጃ ሊሆኑ ይችላሉ። የምታቀርባቸው ሁሉም መረጃዎች ዳኛው ከለላ የፈለግክባቸው ምክንያችን በተሻለ እንዲረዱ የሚያግዙ ይሆናሉ።

ምን እንዳጋጠመህና ከለላ የፈለግህበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማስረዳት እውነታውን መናገርህና በተቻለህ መጠን ሁሉንም መረጃዎችህን ማቅረብ ወሳኝና አስፈላጊ ነገር ነው።

ጉዳይህ የሚታይበት ችሎት እንደተጠናቀቀ ዳኛው የሚወስኑት ውሳኔን ላታውቅ ትችላለህ። ዳኛው ወረቀቶችህን ይዘው ሄደው ካጣሩ በኋላ በጉዳዩ ላይ ውሳኔያቸውን ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ከዛም ውሳኔው ይላክልሃል።

ዳኛው ‘የስደተኞች ኮንቬንሽንን’ እና ‘የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ኮንቬንሽንን’ በጥያቄህ ግላዊ ሁኔታዎች ላይ ተግባራዊ በማድረግ የጥገኝነት ጥያቄህን ይመረምራሉ። ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመቆየት ምክንያት እንዳለህ ጉዳዩን ይመረምራሉ።

ዳኛው ላንተ (እና ለህግ አማካሪህ) እና ለHome Office የተሰጠውን ፍርድ (ውሳኔ) ግልባጭን ይልካሉ። በውሳኔው በሀሪቱ ውስጥ እንድትቆይ ወይም እንድትኖር መናቸውም መስፈርቶችን ስለማሟላትህ የዳኛው እምነት ምን እንደሆነ ይገለጻል። ዳኛው ይግባኝህ ተቀባይነት እንዲያገኝ ወይም እንዳያገኝ (ውድቅ እንዲደረግ) ይወስናሉ። ውሳኔው ከፍርድ ውሳኔው ጀርባ ያለውን ምክንያት የሚያጠቃልል ይሆናል።

## 4B.7 ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ

በአንዳንድ አጋጠሚዎችና ሁኔታዎች አንተና Home Office ሁላችሁም ይግባኝ ልትሉ ትችላላችሁ። ያለኸው UK ውስጥ ከሆነ ይግባኝ የሚቀርብበት ቀነ ገደብ 10 ቀን ሲሆን

ያለኸው እስር ቤት ውስጥ ከሆነ ቀነ ገደቡ 5 ቀን ይሆናል፤ ከUK ውጭ ከሆንክ ደግሞ ይግባኝ የሚቀርብበት ቀነ ገደብ 28 ቀን ነው። የይግባኝ ማቅረቢያ ፈቃድ ማመልከቻ ለጥገኝነትና ኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ከፍተኛ ችሎት መቅረብ አለበት። በዚህ ደረጃ ላይ ላንተ ወይም ለHome Office ጥያቄ ፈቃድ የሚሰጠው በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንደተፈጸመ የሚያረጋግጡ ሁኔታዎች ሲኖሩ ብቻ ነው።

እንግሊዝ ውስጥ ከፍተኛው ችሎት (የኢሚግሬሽንና የጥገኝነት ክፍል) የሚመለከታቸው ጉዳዮች:

- በኢሚግሬሽን፣ በጥገኝነትና በዜግነት ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ በተላለፉ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎችን መመርመር እና፣
- የተወሰኑ የህግ ጉዳይ ምርመራዎች (ኢሚግሬሽን)

ስኮትላንድ ውስጥ ጉዳይህ ለሰበር ፍርድ ቤት ይቀርባል።

ሰሜን አየርላንድ ውስጥ በንግስቲቱ አጥቢያ ፍርድ ቤት ይታያል።

እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ ከህግ አማካሪህ ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ትችላለህ።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ተጨማሪ የይግባኝ መብቶች ሊኖሩ ይችላሉ ለዚህም ከህግ ጠበቃህ ጋር እንድትመካከር እናሳስባለን።

የሕግ አማካሪ እርዳታ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ እባካችሁ በሚቐጥለው ዝርዝር ተገናኙ

የጥገኝነት ምክር (Asylum Advice UK) 0808 8000 622<br>www.asylumhelpuk.org

ኣባካችሁ አስተውሉ: እኛ ስለ የኢምግረሽን ጥገኝነት የጠየቃችሁ የሚመለከት ጉዳይ ልንረዳችሁ አንችልም

## 4B.8 ከይግባኝ በኋላስ ምን ይከሰታል?

አዎንታዊ ውሳኔ ማግኘት - አዎንታዊ ውሳኔ ካገኘህና በጉዳህ ላይ ፈቃድ ካገኘህ Home Office ይግባኝ አያቀርብም ከዛም ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ እንድትቆይ ወይም እንድትኖር ፈቃድ እንዳገኘህ የሚገልጽ የማረጋገጫ ደብዳቤ ከ Home Office ይደርስሃል። (እባክህን የድህረ ውሳኔ ፈቃዶችን አንብብ።)

ተጨማሪ ይግባኝ - አንተ ወይም Home Office በውሳኔው ላይ ይግባኝ ካላችሁና ይግባኝ ለማቅረብ ፈቃድ ከተገኘ ጉዳዩ እንደገና የሚታይበት ቀነ ቀጠሮ ይያዛል። ፍርድ ቤቱ ሌላ ውሳኔ ለማስተላለፍ በሚጠበቅበት ግዜ ውስጥ ጥገኝነት ጠያቂ እንደሆንክ ትቀጥላለህ። ጉዳይህ ብፍርድ ቤት ከታየ በኋላ ጥያቄው ውድቅ ይደረጋል ወይም ተቀባይነት ያኛል።

ምንም ተጨማሪ ይግባኝ አለመኖር – ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ካስተላለፈ በኋላ ይግባኝ የሚቀርብበት ምንም ምክንያት ከሌለ ወይም ይግባኝ የማቅረብ ፍቃድ ከተከለከልክ ያኔ ‘የይግባኝ መብቱን

የጨረሰ (ARE)፣ ትሆናለህ። ይህም ደግሞ የጥገኝነት ጥያቄህ ውድቅ ስለተደረገ ጥገኝነት ጠያቂነትህ አብቅቷል ማለት ነው።

በይግባኝ የተያዘ ምንም ጉዳይ የሌለህ ስትሆን Home Office ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) ትወጣለህ ብሎ ይጠብቃል፡-

Home Office በሚከተሉት ሁኔታዎች ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) ትወጣለህ ብሎ ይጠብቃል፡-

- የጥገኝነት ጥያቄህ ውድቅ የተደረገና ለመቆየት ምንም ፈቃድ ያላገኘህ ከሆንክ፣
- የይግባኝ ሂደቱ መጨረሻ ላይ ከደረስክ፣ ወይም
- የጥገኝነት ማመልከቻህን ከተውከው።

ስለ ሴክሽን 4 እርዳታ በተመለከተ ተጨማሪ ማስረጃ ከፈለጉ ወይም ጠበቃ ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ አሳይለም ሄልፐን በ 0808 8000 622 ደውለው ያግኙዋቸው።

## 4B.9 ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) በፈቃደኝነት ለመውጣት ከመረጥኩስ?

ወደ አገርህ መመለስን ከመረጥክ አንተን ለመርዳት ሁለት አማራጮች አሉ፡-

1) በስደተኞች የእርምጃ ምርጫዎች ፕሮግራም በፈቃደኝነት ለመመለስና የመልሶ መቋቋም ፕሮግራም ከ Home Office (ሆም ኦፊስ) ስር የሚሰራ ድርጅት ለመገናኘት በሚቀጥሎው ዌብ ሳይት አድራሻ ተመልከቱ፡www.gov.uk/return-home-voluntarily

2) በራስህ መንገድ የጉዞ ሁኔታዎችህን ማመቻቸት ትችላለህ። አገሪቱን ለቀህ ከመውጣትህ በፊት ፓስፖርትህን፣ የጉዞና ማናቸውም ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችን ለመቀበል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ለጉዞ ከመነሳትህ በፊት ከHome Office ጋር መገናኘት አለብህ።

## 4B.10 AVR ምንድን ነው?

እርዳታ አግኝተው በፈቃደኝነት የመመለስ (AVR) ፕሮግራም Home Office (ሆም ኦፊስ) ስራው የሚከናወንና የሚመራ ፕሮግራም ነው። በሀገርህ ወይም በሌላ ሀገር የመኖር መብት እንዳለህ ማረጋገጥ ከቻልክ ወደዛ አገር እንድትመለስ ሊረዳህ ይችላል። :

www.gov.uk/return-home-voluntarily
Voluntary Departures Team: 0300 004 0202

## 4B.11 ቤተሰቤ ውስጥ ህጻናት ልጆች ካሉስ?

የቤተሰቡ አባል እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ሰው ሀገሪቱን ለቆ የመውጣት ግዴታ አለበት። Home Office በምርጫዎችህ ዙሪያ ለመወያየት ካንተና ከቤተሰብህ ጋር ለመስራት ዝግጁ ነው። የሚከተሉትን አማራጮች ግምት ውስጥ ያስገባሉ፡

በፍላጎት ስለመመለስ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚከተለው ድረገጽ ላይ መረጃ ያገኛሉ:

www. gov.uk/return-home-voluntarily

በፍላጎት የመመለስ ክፍል ስልክ ቁጥር: 0300 004 0202

የሚጠበቀው ውጤት
በፈቃድህ ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) መውጣት ካልፈለግክ Home Office ወደ ሀገርህ መመለስ እንዳለብህ ደብዳቤ ይጻፍልሃል። ለመመለስ የሁለት ሳምንት ማስጠንቀቂያ የሚሰጥህ ሲሆን ወደ አገርህ ለመመለስ ራስህንና ልጆችህን ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ ማድረግ አለብህ።
የመመለስ ሁኔታህን ራስህ የምታዘጋጅት አማራጭ የሚኖርበት እድል አለ።

የተረጋገጠ መመለስ
የተረጋገጠ መመለስ ተግባራዊ የሚደረገው ወደሃገርህ የምትመለስባቸው ሌሎች አማራጮች ሳይሳኩ ሲቀሩ ነው። የተረጋገጠ መመለስ ደረጃ ላይ ከደረስክ ጉዳይህ የተመላሽ ቤተሰቦች ነጻ ፓነል እንደገና ይታያል። ፓነሉ የማናቸውም ህጻናት ደህንነትን መጠበቅ ግምት ውስጥ በማስገባት ለመመለስ ያለውን የተሻለ አማራጭን ያቀርባል።

Home Office ቤተሰቦች ለጉዞ ከመነሳታቸው በፊት የሚያርፉበት ማዕከል አለው። ማዕከሉ ሴዳርስ (Cedars) ተብሎ የሚጠራና ከጋትዊክ አውሮፕላን ማረፊያ አጠገብ የሚገኝ ነው። የተመላሽ ቤተሰቦች ፓነል ሌሎች ሁሉም የመመለሻ አማራጮች መሞከራቸውን ወይም ተስማሚ አለመሆናቸውን አረጋጦ ይወስናል።

## 4B.12 ወደ ሃገሬ መመለስ ካልፈለግኩስ?

ወደ ሀገርህ ለመመለስ በተዘጋጀ ማንኛውም አገልግሎት መጠቀም ካልፈለግክ ወይም ዩናይትድ ኪንግደምን ለቆ ለመውጣት ምንም ጥረት ሳታደርግ ከቀረህ Home Office አንተን ለማስወጣት አስገዳጅ እርምጃ ይወስዳል። ይህም ማለት ወደ ትውልድ ሃገርህ እንድትመለስ ማስገደድ ማለት ነው።

Home Office አንተን ከዩናይትድ ኪንግደም ለማስወጣት ከፈለገ ጉዳይህ ከHome Office የብሪታኒያ ቪዛና ኢሚግሬሽን ዲፓርትመንት ወደ አገር ውስጥ ጽሕፈት ቤት የኢሚግሬሽን ህግ ማስከበሪያ መስሪያ ቤት (Home Office Immigration Enforcement) ይተላለፋል።

የኢሚግሬሽን ኢንፎርስመንት ሃሰቡ አንተን ከዩናይትድ ኪንግደም ማስወጣት ከሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በዚህ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ማንኛውም የይግባኝ መብትን ያሳውቅሃል። የይግባኝ መብቶችህን የጨረስክ ከሆንክና እዚህ ለመቆየት ምንም ተጨማሪ ህጋዊ ምክንያት ከሌለህ አንተን በግዴታም ቢሆን ከዩናይትድ ኪንግደም ለማስወጣት የሚያስችላቸውን ህጋዊ ሂደት መከተል አለባቸው። ይህ ሂደት አንተን በቁጥጥር ስር ማዋልና አገሪቱን ለቀህ እስክትወጣ ድረስ ለደህንነት አስተማማኝ በሆነ ማእከል በእስረኝነት ማቆየትን ያጠቃልላል። እንደ አማራጭም የኢሚግሬሽን ኢንፎርስመንት አገሪቱን የምትለቅበት ሁኔታ እየተመቻቸ እያለ በተወሰነ ሰዓት በተመደበልህ ቦታ ላይ እየተገኘህ ሪፖርት እንድታደርግ ሊጠይቅህ ይችላል። Home Office የምትባረርበትን ሁኔታ እያመቻቸ እያለ ያለምንም ማስጠንቀቂያ በቁጥጥር ስር

ሊያውልህ ይችላል። :

www.gov.uk/return-home-voluntarily
Voluntary Departures Team: 0300 004 0202

## 4B.13 እስርን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች

Home Office አንተን በእስረኝነት ለማቀየት ውሳኔ በማስተላለፍ ረገድ የሚከተሉትን ወሳኝ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባል። እነሱም፡-

- የቀድሞ የኢሚግሬሽን ታሪክህ
- የትውልድ ሀገርህ
- ግዜያዊ መግቢያን የማክበር ሁኔታህ (በIS96 መሰረት ( ሁል ጊዜ) ሪፖርት ማድረግ አለማድረግህ?)
- ለመሸሽና ለመሰወር ያለህ እድል

## 4B.14 አሁንም ወደሃገሬ መመለሴ አደጋ ይፈጥርብኛል የሚል ግምት ካለኝስ?

የጥገኝነት ጉዳይህ ሙሉ ውሳኔ ያገኘ ከሆነ ላንተ የሚሆኑ ማናቸውም ሌሎች ተጨማሪ አማራጮች ስለመኖራቸውና በጉዳይህ ላይ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የምታቀርባቸው ተጨማሪ ነገሮች ስለመኖራቸው የህግ ምክር ማግኘት ጠቃሚ ነው።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ የህግ አማካሪህን ምክር መጠየቅ አለብህ። ጉዳይህ እልባት ሲያገኝ ሁሉንም ተጨማሪ አማራጮችን ማሳወቅ አለባቸው።

ለHome Office አዲስ የጥገኝነት አቤቱታ ልታቀርብ ትችላለህ። ይህንን ለማድረግም ለ Home Office የምታቀርበው አዲስ ማስረጃ ሊኖርህ ይገባል። የምታቀርባቸው ነገሮች ከዚህ ቀደም ካቀረብካቸው ነገሮች ትርጉም ባለው መጠን የተለዩ ከሆኑ ጥያቄህን እንደ አዲስ ሊያስቆጥሩ ይችላሉ። የሚቀርቡት ማስረጃዎች ትርጉም ባለው መጠን የተለዩ ናቸው የሚባሉት ይዘቱ፡-

(i) ቀደም ሲል ግምት ውስጥ ያልገባ ከሆነ፣ እና

(ii) በፊት ከቀረበው ጋር አንድ ላይ ሲታይ ውድቅ የተደረገው ውሳኔ እንዳለ ሆኖ እንኳ ስኬታማ የሚሆንበት ተጨባጭ እድልን የሚፈጥር ከሆነ።

## 4B.15 ያልተሳካልኝ ጥገኝነት ጠቂ ከሆንኩ የማገኘው ድጋፍ ላይ ምን ይፈጠራል?

እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ጥገኞች የሌሉህ የጥገኝነት ጥያቄህ ውድቅ የተደረገብህ ሰው ከሆንክና የይግባኝ መብቶችህን ተጠቅመህ ከጨረስክ (ARE) ወይም የጥገኝነት ማመልከቻህን ለመተው ከወንክ በጥያቄህ ላይ ሙሉ ውሳኔ ከተላለፈ ከ21 ቀናት በኋላ ድጋፍ የማግኘት መብትህ ታጣለህ። ከHome Office በሚላክልህ ደብዳቤ ያለኸው የHome Office ማረፊያ ቤት

ውስጥ ከሆነ ማረፊያውን ለቀህ እንድትወጣ የ7ቀን ማስጠንቀቂያ ይሰጥሃል።

ቤተሰብህ ውስጥ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ጥገኞች ካሉህ አንተና ቤተሰብህ በፈቃዳችሁ እስክትወጡ ወይም ተገዳችሁ እስክትባረሩ ወይም ጥገኛ ልጆችህ እድሜያቸው 18 ዓመት እስኪሞላ ድረስ ከ Home Office የምታገኘው ድጋፍ ይቀጥላል።

## 4B.16 Section 4 ድጋፍ

**ማመልከቻህ ካልተሳካ ለአጭር ጊዜ የሚሰጥ ድጋፍ**

ድጋፍህ ከተቋረጠ ወደ ሀገርህ ለመመለስ በመዘጋጀት ላይ እያለህ የአጭር ጊዜ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ልትሆን ትችላለህ፡፡'የክፍል 4 ድጋፍ' ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት 1999 ላይ በወታው የኢሚግሬሽንና የጥገኝነት ህግ ክፍል 4 ድንጋጌዎች መሰረት የሚሰጥ ድጋፍ ስለሆነ ነው፡፡ የክፍል 4 ድጋፍ የሚሰጠው የጥገኝነት ጥያቄያቸው ውድቅ ለተደረገባቸው ሰዎች ነው፡፡ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ የክፍል 4 ድጋፍ የጥገኝነት አቤቱታህ በሚታይበት ወቅት ከሚሰጥህ እርዳታ (የክፍል 95 ድጋፍ) የተለየ ነው፡-

- በጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ እርዳታ የለም፡፡ድጋፉ በክፍያ ካርድ መልክ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ይህም 'Azure' ካርድ ተብሎ ይጠራል፡፡የሚያገለግለው የሚከተሉት ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ሱቆች ላይ ብቻ ነው፡- UK - Tesco, Sainsbury, The Co-Operative, Morrisons, Peacocks, Early Learning Centre, Asda, Mothercare, The Red Cross and The Salvation Army.

ለድጋፍ 4 ብቁ ለመሆን የተቀመጡ መስፈርችን ማሟላት አለብህ፡፡ፍጹም ችግረኛና ከሚከተሉት መስፈርቶች መካከል አንዱን ማሟላት አለብህ፡-

1) ከብሪታኒያ ለመውጣት ሁሉንም ተቀባይነት ያላቸው እርምጃዎችን እየወሰድክ ያለህ ወይም ይህንን ልታደርግ በምትችልበት አቋም ላይ ራስህን ያስገኘህ ከሆንክ፣ ወይም

2) አንተ ወይም የቤተሰብህ አባል ጉዞ ማድረግን በሚከለክል አካላዊ ሁኔታ የተነሳ ከብሪታኒያ ለመውጣት መጓዝ የማትችሉ ከሆናችሁ፣ወይም

3) በሴክሬታሪ ኦፍ ስቴት አስተያየት ባሁኑ ሰዓት አስተማማኝ የሆነ ሊመለሱበት የሚችሉበት አስተማማኝ መንገድ ዩናይትድ ባለመኖሩ ዩናይትድ ኪንግደምን ለቀህ መሄድ የማትችል ከሆንክ፣ወይም

4) የጥገኝነት ማመልከቻህ የታየበት የፍርትህ ሂደት ማጣሪያ እንዲደረግ አመልክተህ ፈቃድ ካገኘህ፣ወይም

5) እ.አ.አ 1998 ላይ በወጣው የሰብዓዊ መብቶች ህግ (Human Rights Act) መሰረት የመብቶች ጥሰትን ለመከላከል የመኖሪያ ቤት ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን ናቸው፡፡

**ሁሉም ምክንያታዊ እርምጃዎች**

በዚህ መስፈርት መሰረት ለክፍል 4 ድጋፍ ብቁ ለመሆን ዩናይትድ ኪንግደምን ለቆ ለመሄድ ሁሉንም ምክንያታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆንህን ማሳየት አለብህ፡፡Home Office

በቀረቡልህ ሁሉም አማራጮች እየተከተልክ አይደልህም የሚል እምነት ካደረበት ድጋፍ መስጠቱን ውድቅ ያደርጋል፡፡አንድ እርምጃ 'ምክንያታዊ' ወይም በቂ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ ነው፡ Home Office (ሆም ኦፌስ)። ብዙውን ግዜ በስደተኞች እርምጃ ምርጫዎች ፕሮግራም አማካኝነት በፈቃደኝነት ለመመለስ እንደምታመለክት ጊዜያዊ ፓስፖርት በአስቸኳይ ለማግኘትም (አስፈላጊ ከሆነ) ከሀገርህ ኤምባሲ ጋር እንደምትገናኝና እና ወደ ሀገርህ ለመመለስ Home Office በቀጥታ እንደምታነጋግር ይጠበቃል።

ጠቃሚ ማስታወሻ፡- አዲስ አቤቱታ እንድታቀርብ የሚያስችሉ ምክነያች አሉኝ ብለህ ካመንክ በፈቃደኝነት ለመመለስ ከማመልከትህ በፊት የህግ አማካሪዋቻችሁ ጋር ብትገናኙ በጣም ጠቃሚ ነው። በፈቃደኝነት የመመለስ ማመልከቻ ቆይተህ ብትሰርዘውም እንኳ በአዲሱ የጥገኝነት ጥያቄህ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡2.

2.ጉዞ ማድረግን የሚከለክል አካላዊ ሁኔታ

በዚህ ሁኔታ መሰረት ብቁ ለመሆን በጤና ችግር ምክንያት ጉዞ ማድግ የማትችል ሰው መሆን አለብህ፡፡አንት ወይም ከቤተሰብህ አባላት አንዱ በአካላዊ ወይም በአእምሮአዊ የጤና ችግር ምክንያት ጉዞ ማድረግ እንደማትችሉ ለHome Office ማረጋገጫ ማቅረብ አለብህ፡፡ ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ የህክምና እርዳታ ወይም ክትትል እያገኘህ እንደሆነ ወይም በዶክተርህ አስተያየት መሰረት ጉዞ ማድረግህ እንደማይመከር ወይም ተመራጭ እንዳልሆነ መገለጹን ማሳየት ብቻ በቂ አይደለም፡፡አንተ ወይም ቤተሰብህ ጉዞ ማድረግ እንዳትችሉ የሚያደርግ የጤና ችግር ያለባችሁ መሆን አለባችሁ፡፡

'ጉዞ ማድረግን የሚከለክል አካላዊ ሁኔታ' መኖሩን ለማረጋገጥ መቅረብ ያለበት ማስረጃ፡-

- ጉዞ ማድግ እንደማትችል በግልጽ የሚያስቀምጥ፣ የዚህ ምክንያቶችንና ለጉዞ ብቁ ሳትሆን ልትቆይ የምትችልበት የጊዜ ርዝማኔን የሚገልጽ በሐኪም የተሰጠ የጽሑፍ ሰነድ መቅረብ አለበት
- ከሀኪምህ ጋር በመገናኘት 'የክፍል 4 የጤና ሁኔታ መግለጫ' ቅጽን ከ Home Office ድገጽ በማግኘት ቅጹን መሙላት አለብህ ወይም ከ Asylum Help (አሳይለም ሄልፕ) ጋር በ ቴሌፎን ቁጥር 0808 8000 622 ደውላችሁ የሮርሙ ግልባጭ መላክ ትችላላችሁ።

እርግዝናና ጉዞ ማድረግን የሚከለክል አካላዊ ሁኔታ

በ Home Office ፖሊሲ መሰረት ለመውለድ የተቃረቡ ነፍሰ ጡሮች (ከመውለጃ ቀናቸው ስድስት ሳምንታት አካባቢ የቀራቸው ወይም አስቸጋሪ የጤና ችግር ካለባቸው ደግሞ ከዚህ ጊዜ የበለጠ ያላቸው) ወይም ከስድስት ሳምንት ያነሰ ዕድሜ ያላቸው ጨቅላ ህጻናትን የያዙ እናቶች በቀጥታ (አውቶማቲካሊ) ጉዞ ማድረግ የማይችሉ እንደሆኑ ተቀባይነት ያገኛሉ፡፡

በወሊድ የምስክር ወረቀት፣ በልደት የምስክር ወረቀትና ትወልጃለሽ ተብለሽ ከምትጠበቂበት ጊዜ ከስድስት ሳምንት በፊት የምታመለክቺ ከሆንሽ የህክምና ማስረጃሽንና የእርግዝና ማረጋገጫውን ማቅረብ ግዴታ ነው፡፡

3. አስተማማኝ የመመለሻ ጉዞ መስመር አለመኖር
ይህ መስፈርት ዩናይትድ ኪንግደምን መልቀቅ በማይችሉ ሰዎች ላይ ተግባራዊ አይሆንም ምክንያም በሴክሬታሪ ኦፍ ስቴት አስተያየት ባሁኑ ሰዓት አስተማማኝ የሆነ ሊመለሱበት የሚችሉበት ምንም መንገድ የለም።

4.የፍርድ ሂደት ማጣሪያ ማመልከቻ
የህግ አማካሪህ የጥገኝነት ጥያቄህ ላይ የተላለፈ ውሳኔን በተመለከተ የፍርድ ሂደት ማጣሪያ ጥያቄን የሚያቀርብ ከሆነ በመጀመሪያ ሂደቱን ለመቀጠል የሚያስፈልገውን ፈቃድ ለማግኘት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ማመልከት አለባቸው፡፡ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ፈቃድ ካገኛችሁ በኋላ በዚህ መስፈርት መሰረት በክፍል 4 የሚሰጠውን ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ትሆናለህ። በScotland (ስኮትላንድ) አገር የሚኖሩ ከሆነ እና በፍርድቤት ያቀረቡት ማመልከቻ ካለ በሕግ መሰረት፡ በዚሁ ሕግ ክፍል ካገሩ ሳይለቁ እንዲቆዩ ፍቃድ እንዲሰጣችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።

‘የፍርድ ሂደት ማጣሪያ ማመልከቻን’ ለማረጋገጥ የሚያስፈልግ ማስረጃ፡-
መቀጠል እንደምትችሉ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠ ፈቃድን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፡ ማመልከቻው ወድ ፍርድ ቤት እደተላከ በ በScotland (ስኮትላንድ) ውስጥ የሚያሳይ ማረገገጫ ሊኖራችሁ ይገባል።

5.የሰብዓዊ መብት ጥሰት
Home Office እርምጃው በእርስዎ ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን የሚያስከትል ከሆነ የሚሰጠውን ድጋፍ መቋረጥ አይችልም፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች ችግረኝነት በአንድ ሰው ሰብዓዊ መብቶች ላይ እንደሚፈጸም የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚቆጠር ቢሆንም የጥገኝነት ጥያቄው ውድቅ የተደረገበትና ዩናይትድ ኪንግደምን ለመልቀቅ ሁሉንም ጥረት አላደረገም ተብሎ የሚታሰብ ግለሰብ ድጋፍ ወይም እርዳታ የማግኘት መብት የለውም፡፡የዚህ ምክንያትም በፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረት እነዚህ ሰዎች ችግረኛ የሆኑት በምርጫቸውና በፍላጎታቸው ስለሆነ እርዳታ የማግኘት መብት የላቸውም፡፡Home Office የሚሰጠውን በማቋረጡ ምክንያት በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ኮንቬንሽን (European Convention of Human Rights, ECHR) ድንጋጌዎች መሰረት የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚፈጽም ሆኖ ከተገኘ እርዳታ መስጠቱን ይቀጥላል፡፡

ለምሳሌ አዲስ የጥገኝነት አቤቱታ በማቅረብህ ሂደቱ ያልተጠናቀቀ የሚሆን ከሆነ በዚህ ክፍል ማመልከት ትችላለህ፡፡በተመሳሳይ መልኩም የፍርድ ሂደት ማጣሪያ ማመልከቻ ገብቶ ፈቃድ ያልተሰጠ ከሆነ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ቤተሰብህ የተወሰኑ አባላቱ ድጋፍ በመከልከላቸው ምክንያት የሚበታተን ሆኖ ከተገኘ በዚህ ክፍል መሰረት ድጋፍ ጥያቄህን ማቅረብ ትችላለህ።ወደ አገራችሁ ልትመለሱ ይማይስችላችሁ ተጨማሪ መረጃ ወይም ምንክንያት አለኝ ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ፡ በአስቸከዋይ ከየሕግ አማካሪያችሁ ተኘናኝታችሁ ምክር መቀበል አለባችሁ። ከሆም ኦፊስ ጋር ያልዎት ጉዳይዎ በደህንነትዎ መጠበቅ ላይ ያልተመሰረተ ከሆነ የድጋፍ እርዳታ አይገባዎትም። ምክንያቱም እግሊዝ አገር የመቆየት መብት ስለሌሎት እዚህ ሆነው ችግረኛ ከመሆን ይልቅ ከእግሊዝ አገር ለቀው መሄድ ስለሚችሉ።

- አዲስ አቤቱታ ስለመቅረቡ ማረጋገጫ

- የልደት የምስክር ወረቀቶች፣ የቤተሰባዊ ሕይወት ማረጋገጫ
- ለከፍኛው ፍርድ ቤት የቀረቡ ሰነዶች ግልባጭ ወይም ኮፒ

ስለ ሴክሽን 4 እርዳታ በተመለከተ ተጨማሪ ማስረጃ ከፈለጉ ወይም ጠበቃ ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ ኣሳይለም ሄልፐን በ 0808 8000 622 ደውለው ያግኙዋቸው።

## 4B.17 ችግረኛ መሆኔን ለማረጋገጥ ምን ማድግ አለብኝ?

Home Office አንተን እንደ ችግረኛ የሚወስድህ ‘በቂ መጠለያ’ ማግኘት የማትችል ሰው ከሆንክ ወይም ‘ለኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን’ (ለምሳሌ ምግብ፣ ብርሃንና ሙቀት) ባሁኑ ሰዓት ወይም በቀጣዮቹ 14 ቀናት ውስጥ ልታሟላ የምትችልበት መንገድ የሌለህ ከሆንክ ነው፡፡

ባሁኑ ሰዓት ‘ቤት አልባ’ የጎዳና ተዳዳሪ እንደሆንክ ወይም የጎዳና ተዳዳሪ የምትሆንበት አደጋ እንደተደቀነብህ ማሳየት የለብህም፡፡በቂ መጠለያ እንደሌለህ ወይም በቀጣዮቹ 14 ቀናት ውስጥ ለኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮችን ለማሟላት የሚስችል አቅም እንደሌለህ ማሳየት በቂ ነገር ነው፡፡

ችግረኛ መሆንዎ ይጣራል ይህ ማለት ደግሞ ኣመልካች ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል። ‘ችግረኛነትን’ ለማረጋገጥ የሚያስፈልግ ማስረጃ፡-

- የሚደረግልህ ድጋፍ ከተጠናቀቀ በኋላ የቆየህባቸው አድራሻዎች ዝርዝርን እንዲሁም በእያንዳንዱ አድራሻ ለምን ያክል ግዜ እንደቆየህና ይህ ድጋፍ ካሁን በኋላ ለምን ሊቀጥል እንደማይችል ያለውን ምክንያት ማቅረብ አለብህ፡፡
- በቅርብ ግዜያት የኖርክበት ቦታ የት እንደሆነና ካሁን በኋላ እዛ ቦታ ላይ መኖር የማትችልበት ምክንያት ምን እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ (በጓደኛህ ወይም በዘመድህ የተጻፈ ደብዳቤ) ያለፉትን ስድስት ወራት የሚያጠቃልል መሆን አለበት።
- ያገኘኸው ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድጋፍ ወይም የበጎ አድራጎት እርዳታ ለማግኘት ያደረግከው ሙከራ ማስረጃ
- ባለፉት 6 ወራት ውስጥ የተሰጠህ ማንኛውም የባንክ ግብይት መግለጫ (ካለህ) ግልባጭ
- ብቻሽን ልጅ የምታሳድጊ ወላጅ ከሆንሽ ደግሞ ከልጅሽ አባት የልጅ መሳደጊያ ድጋፍ ለማግኘት ያደረግሽውን ሙከራ የሚያሳይ ማስረጃ እንድታቀርቢ ልትጠየቂ ትችያለሽ
- ከዚህ በፊት የስራ ፈቃድ ከነበረህ ወይም በህገ ወጥ መንገድ ስራ ከሰራህ የቅርብ ጊዜ P60 እና/ወይም የደመወዝ መክፈያ ስሊፖችን እንዲሁም ከሆነ ግዜ ጀምሮ በመስራት ላይ እንዳልሆንክ ወይም ስራ የምትሰራበት ፈቃድ እንደሌለህ የሚያሳይ ማስረጃ እንድታቀርብ ልትጠየቅ ትችላለህ
- የምትኖረው ከግለሰብ በተከራኸው መኖሪያ ቤት ውስጥ ከሆነ የኪራይ ስምምነቱና ቤቱን እንድትለቅ የቀረበልህ ማንኛውም ጥያቄን
- ከዚህ ቀደም ዋነኛ ጥቅማ ጥቅሞችን ወይም እርዳታዎችን ታገኝ ከነበረ ከሆነ ግዜ ጀምሮ ያንን እርዳታ የማግኘት መብት እንደሌለህ የሚያሳይ ማስረጃን (ለምሳሌ DWP የጻፈልህ

ደብዳቤ)

• ከዚህ በተጨማሪም በፊት ይሰጥህ የነበረው ድጋፍ ከተቋረጠበት ግዜ ጀምሮ ኑሮን እንዴት እየገፋኸውን እንደሆንክ የሚገልጽ ግላዊ መግለጫህን አዘጋጅተህ ብታቀርብ ጠቃሚ ነገር ነው፡፡እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ መረጃዎችን ማቅረብ ለማይችሉ ሰዎች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ

## 4B.18 የክፍል 4 ድጋፍን ለማግኘት እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

የክፍል 4 ድጋፍን በተመለከተ (ብቁነትን ጨምሮ) ተጨማሪ መረጃዎችን ወይም ምክር ማግኘት ከፈለግክ የጥገኝነት እርዳታ ክፍል 0808 8000 622 ጋር መገናኘት አለብህ፡- ድረ ገጽ www. asylumhelpuk.org ወይም የጥገኝነት ድጋፍ መስመር

የክፍል 4 ድጋፍን ለማግኘት ለማመልከት ከወሰንክ እና በማመልከቻ ቅጹ ላይ እገዛ ማግኘት ከፈለግክ የጥገኝነት እርዳታ ክፍል ጋር መገናኘት አለብህ፡-የጥገኝነት ድጋፍ ማመልከቻ UK ድረ ገጽ www.asylumhelpuk.org Asylum Support Application UK ወይም የጥገኝነት ድጋፍ መስመር (የድጋፍ ማመልከቻዎች) 0808 8000 623 ወይም ደግሞ ድረ ገጽ www.asylumhelpuk.org ገብታችሁ ተመለከቱ።

ድጋፍ ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ ሁሉም መረጃዎች እንዳሉህ ማረጋገጥ አለብህ፡፡

ጠቃሚ መረጃዎች፡-ድጋፍ ለማግኘት የማይችሉበት ጊዜ ያለ ሲሆን ይህም የሚሆነው Home Office (ሆም ኦፊስ) ማመልከቻህን እስኪያስፈጽም ድረስ ነው። Asylum Help (አሳይላም ሄልፕ) ስለዚህ እርዳታ ለማግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ ሊረድዋችሁ ይችላሉ። ሆኖም ግን ምንም ገንዘብ እንዴላችሁ ገቢ እንደሌላችሁ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ አለባችሁ። ወይም ደግሞ እርዳታ ለማግኘት የሚያስፈልግ ነገር ማሙአላት አለባችሁ።

Asylum Help (አሳይላም ሄልፕ) ስለሁኔታችሁ የሚመለከት ምርመራ ያደርጋሉ፡ የቀረባችሁት መረጃዎች Home Office (ሆም ኦፊስ) እንድታቀርቡት የሚጠይቃችሁ መረጃ በቂ ነው ወይስ ተጨማሪ ማቅረብ የሚያስፈልጋች እርዳታ ለማግኘት ይረድዋችዋል። ይህ ከደረሰን በኃላ እኛ ፎርሙን ሞልታችሁ እንትልኩት እንረዳችዋለን። ሆኖም ግን Home Office (ሆም ኦፊስ) በቂ መረጃ አልደረሰንም ምንም ዓይነት ሌላ ገቢ እንደሌላችሁ የሚያሳይ በቂ መረጃ አልደረሰን ብሎው መልስ ከሰጡ፡ወይ አልተቀበልናችሁም ብለው ጉዳያችሁ ይዘኡጉታል ወይም ደግሞ ተጨማሪ መረጃ አንድታቀርቡ ይጠይቅዋችዋል።

## 4B.19 Section 4 ስለ ድጋፍ የሚቀርብ ይግባኝ

ለክፍል 4 ያቀረብከው ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገና ከዛም ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ (ለጥገኝነት ድጋፍ ችሎት) ይግባኝ የማቅረብ መብት ካህ፡፡Home Office ድጋፍ የማግኘት ጥያቄህ ውድቅ እንደተደረገ የሚገልጽ ደብዳቤ ይልክልሃል፡፡በዚህ ደብዳቤ ጥያቄህ ውድቅ የተደረጉባቸው መነሶች/ምክንያቶች ይገለጻሉ።
ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ባሉት ሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የይግባኝ አቤቱታዎች መቅረብ አለባቸው፡፡ይግባኝ በተመለከተ እገዛ ለማግኘት በተቻለህ መጠን በፍጥነት ከጥገኝነት ድጋፍ ሰጪ ክፍል (Asylum Help) ጋር መገናኘት አለብህ፡፡የጥገኝነት ምክር (Asylum Supoort) UK ድረ ተጨሪ እርዳታ ካስፈለጋችሁ በሚቀትለው ጋር Asylum Support Appeals Project (አሳይለም

ሱፖርት ፕሮጀክት) ደረ ገጽ www.asaproject.org

## 4B.20 በሁኔታዎች ላይ የሚከሰቱ ለውጦች

በሁኔታዎችህ ላይ የሚከሰቱ ለውጦችንና ወቅታዊ መረጃዎችን ለ Home Office፣ ለፍርድ ቤቶች እና ለህግ አማካሪህ (ካለህ ማለት ነው) ማሳወቅ ጠቃሚ ነገር፡፡ይህም በጉዳይህ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡የአድራሻ ለውጥህን ሳታሳውቃቸው ከቀረህ ጠቃሚ የሆኑ የፍርድ ቤት ደብዳቤዎችን ሳታገኝ ልትቀር ትችላለህ፡፡ህጻን ልጅ እያለህ ይህንን ሳታሳውቅ ከቀረህ ህጻኑ ልጅ የጥገኝነት ማመልከቻህ ውላይ አይካተትም፡፡Home Office በሚከተሉት ነገሮች ላይ የሚደረግ ላይ ለውጥን እንዲያውቅ መደረግ አለበት፡-

- የስም ለውጥ ስታደርግ፣
- በስርህ የሚተዳደሩ ጥገኞች መካከል ማናቸውም 18 ዓመት ሲሞላቸው፣
- አድራሻህን ወደ ሌላ ቦታ ስትቀይር፣
- ትዳር ስትመሰርት ወይም ስትፋታ ወይም ከትዳር አጋርህ ጋር ስትለያይ፣
- ሆስፒታል ተኝተህ ስትታከም፣
- አንቺ ወይም የትዳር አጋርህ ስታረግዝ ወይም ልጅ ስትወልድ፣
- ከልጆችህ መካከል ማናቸውም ትምህርታቸውን ሲያቋርጡ ወይም ከቤት ሲወጡ፣
- ሌላ ማንኛውም የቤተሰብ አባል ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ አንተ ጋር መኖር ሲጀምር ወይም አንተን ትቶ ሲሄድ፣
- ሌላ ማንኛውም ሰው አንተ ጋር ሲጀምር ወይ አንተን ትቶ ሲሄድ፣
- እስር ቤት ስትገባ፣
- ከዚህ በፊት ያላሳወቅኸን ገንዘብ ትቀበል ወይም ገንዘብ የምታገኝበት መንገድ ስታገኝ፣
- የሆነ ነገር ከሸጥክ በኋላ ገንዘብ ትቀበል ወይም ገንዘብ የምታገኝበት መንገድ ስታገኝ፣ ወይም
- ከሆነ ጊዜ በኋላ የመኖሪያ ቤት ድጋፍ እንድናደርግልህ የማትፈልግ ስትሆን፡፡

ከላይ የተገለጹት ነገሮች በጥገኝነት ድጋፍህ ላይ አንድምታ ለኖራቸው ወይም ለፍርድ ቤት/ ለህግ አማካሪህ ልትነግራቸው የሚገቡ ሊሆኑ ይችላሉ; Asylum Help (አሳይለም ሄልፕ) ለ Home Office (ሆም ኦፊስ) የጥገኝነት ክፍል በላይ የተጠቀሰው ሁኔታችሁ ለውጥ እንዳለ ሊያሳውቅላችሁ ይችላል። ሆኖም ግን በጣም አስፈላጊ ነው እናንተ ለየኢሚግረሽን ክፍል ስለዚሁ ለውጥ Home Office (ሆም ኦፊስ)/ፍርድ ቤት ስለዚሁ ለውት እንድታሳውቅቀዋቸው። የሕግ አማካሪ (ጠበቃችሁ) ስለዚሁ ጉዳይ ሊረዳችሁ ይችላል።

የዚህን ክፍል Asylum Support (አሳይለም ሳፖርት)የሕግ አማሪ ጋር ለማገናኘት ምክር አስመልክቶ ማንኛውም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሚከተለው ክፍልን ያነጋግሩ።

www.asylumhelpuk.org

Asylum Advice UK (አሳይለም አድቫኢስ ዩከው) ይጥገኝነት ጉዳይ ምክር የሚሰጥ 0808 8000 622፣

Asylum Support Application UK (አሳይለም ሳፖርት አፕሊከሽን) የጥገኝነት ድጋፍ መስመር (የድጋፍ ማመልከቻዎች) 0808 8000 623